ከትንሳዔ ቁጥር2 ራድዮ የተወሰደ

## ለማይቀር ውርደት መከናነብ - ትርፉ ሸክም ነው!

የተወደዳችሁ ኢትዮጵያውያን!

እንኳን ለአዲሱ ዘመን በሰላም አደረሳችሁ!

የዘመን ለውጥ የአስተሳሰብ ለውጥንም ይዞ እስካልመጣ ድረስ ቁጥር ብቻ ከመሆን አያልፍም። ዓመቱን ስንለውጥ የትግሉንም ይዘት ስንገመግም ምን ተሰራ ብለን ስንቃኝ፤ የምናገኘው መልስ ኢትዮጵያዊው ግንዛቤውን እያሰፋ በወያኔ ስር መኮልኮሉን እየተጠየፈው መሄዱን ነው። ወያኔ ህሊና ያላቸው ደጋፊዎች ያጣበት ዘመን ላይ መሆኑ ነው የሚታየው። ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በንፅህና ከተጓዙ፤ ደጋፊዎቻቸውም በነፃና በግልፅ ድጋፋቸውን ማድረግ ከቻሉ፤ የጓሮ መንገደኛ እግሩን በሾህ ከማስወጋት ይገላገላል። ህዝባዊ የሆነው ቅንጅት በሀገር ውስጥ እንዳይንቀሳቀስ በወያኔ ተፅዕኖ ሲደረግበት አመራር ላይ የነበሩ አባላቱም ተገነጣጥለው የራሳቸውን መንገድ ለመሄድ ሲወስኑ የየራሳቸው ምክንያት ነበራቸው። ሆኖም ውሳኔያቸው አስቀድሞ የተፈጠረውን ችግር የሚፈታ መሆን ይገበዋል። ለምሳሌ የነወይዘሪት ብርቱካን ፓርቲ ስሙ "አንድነት" ተብሎ እንዲጠራ ነው የተደረገው።

እንደሚታወቀው ቀደም ብሎ በክቡር ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ የተቋቋመው ድርጅት መጠሪያው "አንድነት" የሚል ነው። ጋዜጣው እንኳ ሳይቀር የሚዘጋጀው "አንድነት ጋዜጣ" በሚል ስያሜ ነው። ከዚያም በሁዋላ ቢሆን በቀጣይነት የመጣው የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ ተብሎ ሲመሰረት "አንድነትን" መነሻ መፈክሩ አድርጎ ነው በህግ ሲንቀሳቀስ የቆየው። ያ ሳይሻር ነው ዛሬ ሌላ "አንድነት ፓርቲ" በሚል እንዲቋቋም የተደረገው። ለነገሩ ህዝቡ አንድነት በተነሳ ቁጥር ፕሮፌሰር አሰራትንና ድርጅታቸውን ነው የሚያስታውሰው፡ የኢትዮጵያ አንድነት የሚለውን መንፈስ ነው የሚረዳው። አንድነትን ከሀገርና ከህዝብ ጋር አያይዞ ነው የሚያውቀው እንጂ አንድነትን ከፍትህና ከዲሞክራሲ ጋር አይደለም። ምክንያቱም በፍትህም ሆነ በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ አንድነት ባዶ ቃል ነው። ፍትህም ሆነ ዲሞክራሲ የልዩነት መገለጫዎች ናቸውና። ፍትህን በግለሰብ ዲሞክራሲን በማህበረሰብ ጥያቄ ላይ ለያይቶ ማየት ስለሚያስፈልግ። አንድነት የሚለው ቃል ይበልጥ ትርጉም የሚኖረው ከህዝብና ከሀገር ጋር ባለው ስሜት ውስጥ ነው። በዚህ በኩል ችግር ላይኖር ይችላል። ሆኖም ግን ቅንጅትን እነ አቶ ጫሚሶ ወስደው ውዥንብር መፍጠራቸው ችግር እንደፈጠረ እየታወቀ፤ ሌላ አሻሚ የሆነ ስም ለመጠቀም መወሰኑ አዋቂዎች ባለማወቅ ያደረጉት ስህተት ነው ብሎ ለመቀበል ብዙው ሰው ይቸገራል።

አዲሱ ፓርቲ ስሙን "ፍትህ" ወይም "ዲሞክራሲ ፓርቲ" ብሎ ቢጠራው ለህዝብ ግልፅ በሆነ ነበር። ሊፈጠር የሚችለውንም አለመግባባት ባስወገደ ነበር። እናም ይህ አይነቱ ጉዳይ ለምን ሆነ ብሎ መጠየቅ ጠብን ማጫር መስሎ የሚታያቸው ካሉ




EthioLion.com

ረጋ ብለው ሁኔታውን ሊመረምሩት ይገባል። በጣም የሚያስገርመው ግን የወያኔ ምርጫ ቦርድ “አንድነት” በህግ የተመዘገበ የሌላ ፓርቲ ስም እንደሆነ እያወቀ፣ መፍቀዱ ነው። የተደበቀው ተንኮል የት ዘንድ ነው ያለው ብለን መፈተሽ የግድ ይላል። ወያኔ ያለምንም ማመንታት ድጋሚ ስም ሲሰጥ ከ 15 ዐመት በማያንስ አንድነት ፓርቲ ህጋዊነት ያለው መሆኑን እያወቀው ነው። አመልካቾቹም ይህን ጉዳይ ባለማወቅ አደረጉት ለማለት የሚቸግረውም በዚህ ምክንያት ነው። ብቻ በጠራ አሰላለፍ አቅዋምን ግልፅ አድርጎ መጓዝ ያስቸገረበት ሁኔታ ያስገርማል። አሁንም ያንኑ የተለመደ የመሸዋወድ ካባችንን ለብሰን ነው ለአዲስ ዓመት ላዲስ ትግል የምንዘጋጀው? አሁንም ይኸንኑ መሸፋፈኛ ጋቢያችንን ተከናንበን ነው ስለ ግልፅነት የምናወራው? ስለ ህብረት የምንደሰኩረው? ለምን ከሚያጋጩን ይልቅ በሚያስማማን ላይ ማተኮሩን አናንቀን አየነው።

በአሁኑ ወቅት እኛ ኢትዮጵያውያን እንደህዝብ በመኖርና ባለመኖር መካከል የምንገኝ ነን። ዛሬ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ያለው ነዋሪ ኢትዮጵያዊ በተለይም በጠረፉ አካባቢ ያለው ያለፍላጎቱ በሱዳን ዜግነት ስር እንዲተዳደር እየተበየነበት ነው በወያኔ። ባድመ ከዚያ ሁሉ የህዝብ ዕልቂት በሁዋላ ለሻዕቢያ ተሰጥቷል በወያኔ። ኤኮኖሚው ወያኔ እንደሚያወራው ሳይሆን በልቶ ማደር እንኳ ያዳገተበት ሁኔታ ላይ ተደርሷል። እናም እኛ ስም እየቀያየርን ለመሸዋወድ እንቅልፍ ሳይወስደን ይነጋል።

በእርግጥ ኢትዮጵያን እናድን ሲባል እያንዳንዱ ዜጋ ሀላፊነቱን አውቆ የድርሻውን ያድርግ ማለት ነው። ለ17 ዓመታት የተግማማ የወያኔ የዘር ፖለቲካን፣ የበሸቀጠ አገዛዝን፣ ሙስናን፣ ተንኮልን፣ ሸርን ለኔ ብቻ ማለትን፣ በሌላ መልኩ እናድሰው ማለት ግን አይደለም። ወያኔን እናስወግድ ሲባል! ኢትዮጵያውያንን ሲያንገላታ፣ ንፁሃን ዜጎችን ሲገርፍና ሲገድል የነበረን አጅበን ለስልጣን እናብቃ ማለት አይደለም። ዛሬ በጎሳ ስም ተወሽቆ፣ በፖለቲካ ስም አጭበርብሮ ለመውጣት በንፁህነት ለመታየት የሚሞክር ካለ ታሪኩን በስልቻ ቋጥሮና በጀርባው አዝሎ የሚጓዝ መሆኑን ማወቅ ይገባዋል። ኢትዮጵያን እናድን ሲባል አፋኝን ገዳይን እሹሩሩ እንላለን ማለት አይደለም። ወያኔ ንቆት የገፈተረውን አዋቂ አድርገን እንንከባከባለን ማለትም አይደለም። ስለዚህም ነው፣ የሻዕቢያን የጦር አጋርነት፣ የእነ ሰዬ አብርሃምንና ገብሩ አስራትን ኢትዮጵያዊ የሀገር ፍቅር ስሜት፣ የእነ አብርሃም ያየን የፖለቲካ ታንቲራ፣ የነኦነግን የትብብር ጥሪ! የግንቦት 7ን ከሲዳማ ነፃ አውጭ ነኝ ባይ ቡድን እንዲሁም ከኦጋዴን ነፃ አውጭ ነኝ ባይ ቡድን ጋር ተጎዳኝቶ በሻዕቢያ ተደግፎ ኢትዮጵያን አድናለሁ የማለትን ጥሪ ለመቀበል የምንቸገረው።

ኢትዮጵያ ዳነችም ጠፋችም ተሟጋቿ ህዝቧ እንጂ ሌሎች ሊሆኑ አይችሉም። ኢትዮጵያዊ ጠረኛ ተብሎ ባንዳንድ አዋቂ ነን ባዮች ሲተች የሚደመጠው፣ ሀገሩን ያስከበረው በልመና ሳይሆን፣ ከጠላት ጋር በመሞዳመድ ሰይሆን፣ ለባዕድ አሽከር ባለመሆን በራሱ ቆርጦ ስለተዋጋ ብቻ ነው። አንዲት ኢትዮጵያ ወይም ሞት ብሎ በጀግንነት በመታገሉና ነፃ ሀገርን በማቆየቱ ብቻ ነው የዛሬው ስም አጥፊዎቹ ከውስጥም ከውጭም የሚረባረቡበት። ሌላ ምክንያት የላቸውም። ኢትዮጵያን ለማዳን መንገዱ ግልፅ ነው። ቆራጥነት፣ የሀገር እንጂ የስልጣንና የጥቅም ተገዥ

EthioLion.com

ያለመሆን ከብዙ መመዘኛዎች መካከል አንዱ ነው። ከዚያ ውጭ በመቻቻል ስም፤ በየዋህነት ከራስ አጥፊ ጋር ተቀላቅሎ መጓዝ ብልህነት አይደለም። በዚያ መንገድ ተጉዞም ህዝብ የስልጣኑ ባለቤት አልሆነም። ወደፊትም ሊሆን አይችል። ባለመሆኑም ዳግም ያምሮታሞችና፤ የከዳተኞች መድረክ በመፍጠር ሀገርን ለውርደትና ለጥፋት መዳረግ ተገቢ አይሆንም። አሳሳቾች መልካቸውን በቀየሩ ቁጥር የኢትዮጵያ ልጆች ቀጤማ ጎዝጉዘው ይቀበሉናል ብለው ካሰቡ ተሳስተዋል።

ወያኔን እንታገል ማለት እኮ! ቀደም ሲል የጎሰኝነትን መፈክር አንግበው ለቀበሌአቸው እንጂ ለኢትዮጵያ ህልውና ቅንጣት ታህል ስሜት ያላሳዩትን ጎጠኞች ከጎናችን አሰልፈን በትግል ሜዳ ላይ እንወናከር ማለት አለመሆኑ ሊስተዋል ይገባል። ወያኔን እንታገል ሲባል የቀፈቀፋቸውን ጫጩቶች በጉያችን ሸጉጠን ሙቀት እየሰጠን እናሳድግ ማለት እንዳልሆነ ሊገባን ይገባል። ኢትዮጵያን እናድን ስንል እውነተኛ አፍቃሪ ልጆቿ ከጎጥ/ ከጎሳ በላይ ውለው፤ በመሰባሰብ ለአንድነቷ፤ ለባንዲራዋ፤ ይሚገቱላት ማለት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። እንቻቻል ሲባል በህዝብ ላይ ግፍ የፈፀሙ በድርጊታቸው ተፀፅተው፤ ህዝብን ይቅርታ ጠይቀው፤ ምህረት ያገኙ የሚል ነው። ያ ባልሆነበት ሁኔታ ወያኔን ተባብረን እንጣል ከሚሉት ጋር መተባበር በሀገርና በህዝብ አንድነት ላይ መቀለድ ነው የሚሆነው። የትግሉን መግኒቅ በእጃቸው ጨብጠው ወደ ማንፈልገው አቅጣጫ እንዲያጓጉዙንም ፈቃድ ሊሰጣቸው አይገባም።

ወያኔ የማጭበርበር ታክቲኩ ከጊዜ ወደጊዜ እየረቀቀ የሚሄድ በመሆኑ የታጋዩም የምርመራ ዓይን ያንኑ ያህል ሳያንቀላፋ መከታተሉ የማይቀር ነው። በዚህ ዙሪያ የሚነሳ ጥያቄ አተካራ ለመፍጠር በመፈለግ የሚደረግ ሳይሆን ትግሉ በጥራት እንዲራመድ ከመሻት የሚመነጭ ነው። ግልፅነት የተሞላበት አካሄድ እንዳይፈጠር መሰናክል የሚሆኑ ግለሰቦችን አበጥሮ አውቆ የትግል አባወራ የመሆን ፍላጎታቸውን ማጨናገፍ ህዝባዊ ትግልን ያጎለብታል የሚል ነው። የወያኔ ኤኮኖሚ ዕድገት ህዝብ ማስራብ መሆኑን ሊያዩት ያልቻሉ የወያኔ አጋፋሪዎችን፤ በህዝብ ውስጥ ገብተው ተሸፋፍነው መርዛቸውን እንዲረጩ መፍቀድ ተገቢ አይሆንም የሚል ነው። የኢትዮጵያን ህዝብ ትግል መርጃው አንደኛው መንገድ ይኸ ነው። ያዩትን ላላየው ማሳየት። የሰሙትን ላልሰማው ማሰማት። ወያኔን ለኢትዮጵያ ልማት የቆመ አስመስለው ባዶ ጡሩምባ የሚነፉትን ትርፉ ትንፋሽ መጨረስ እንደሆነ ማስገንዘብ። እርስ በእርስ መታገል አያስፈልግም ለሚሉ ክፍሎች አስቀድመው ወያኔ ማነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ መሻት ይኖርባቸዋል።

ለብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ወያኔ ማለት ትግሬ ማለት አለመሆኑ ግልፅ ነው። ሊሆንም አይችልም። ወያኔ ማለት የወያኔን ዓላማ ለማሳካት ደፋ ቀና የሚለው ለሆዱ ያደረ አማራ፤ ኦሮሞ፤ ጉራጌ፤ ወላይታ ወዘተ ሁሉ ነው። ኢትዮጵያዊው ወያኔን ብቻ ሳይሆን ጠባብ አስተሳሰብ ያላቸውን ሁሉ መታገል አለበት። ተዋዝተው የሚያዋዙትን ሁሉ መታገል አለበት። ኢትዮጵያዊው የህሊናን ባርነት መዋጋት ካልቻለ ወያኔ ላዘጋጀለት የመከራ ዘመን በፈቃደኝነት እጁን ያሳሰረ መሆኑን መገንዘብ ይገበዋል። ወያኔ እህቶቻችንን ለዐረብ ሀገራት ባርነት በሽያጭ ለማቅረብ መዋዋሉን እየተገነዘበ፤ በዘመናዊ ባርነት ስርአት መሰረት ኢትዮጵያ ከማንኛውም አፍሪቃ አገር ግምባር ቀደም ሆና ባሮችን በማቅረብ ረገድ ቀዳሚውን ስፍራ

EthioLion.com

እንድትይዝ መደረጓን እያወቀ፤ ወያኔን በአንዱ ወይም በሌላው መልኩ የሚደግፍ፤ ህዝብ ተባብሮ እንዳይነሳ መሰናክል የሚፈጥር ሁሉ ወዳጅ ነው ተብሎ ሊፈረጅ አይችልም። ስለዚህም መታገል ያስፈልጋል።

የተከበራችሁ የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች!!

ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማዋረድ ዘርፈ ብዙ ፕሮግራም ነድፎ የሚንቀሳቀስ ሀይል ነው። ይህ ገዢ ሀይል ሰዎችን ወደ አሜሪካና ወደ አውሮጳ በማስወጣት የኤኮኖሚ ትርፍ እያጋበሰ ይገኛል። የእንጀራው ሺያጭ በአሜሪካ የሚገኙ ጀግኖች የኢትዮጵያ ልጆች በተለይም ዓለም አቀፉ የሴቶች ማህበር በመታገሉ ዕድገቱን እያሽመደመደው ነው። አውሮጳ ተጨባጭ የሆነ ትግል በዚህ በኩል ማድረጉን አላስመሰከረም። አሁንም እንጀራን ገዝቶ የመብላት ደምበኛ ሆኗል። አሁንም የንክኪ የጓደኝነት የዝምድና ፖለቲካውን እያራመደ ነው። ፖለቲካን ከቤተሰብ ቁርኝት እስካላወጣ ድረስ፤ በእምነትና በህዝብ ወገናዊነት ስሜት እስካላካሄደ ድረስ ወያኔን እቃወማለሁ ማለት ከቂም በቀል የፀዳ አይሆንም። የወያኔን እንጀራ እየገዛ ወገኑን የሚያስርበው ሰው ከህሊናው መምከር ይኖርበታል። ዛሬ በትግሉ ውስጥ ውሃ እየረጩ ያሉት የወያኔ ስደተኞች፤ በወያኔ ፕሮጀክት ውስጥ ተካተው እንደሚገኙ ድብቅ አይደለም። ወያኔ በቅርቡ በዓለም አቀፍ ደረጃ የአክሱምን ሀውልት አስመልክቶ ታላቅ የመጨፈሪያ በዓል ሊያዘጋጅልን ደፋ ቀና እያለ መሆኑ ታውቋል። ይህ ገንዘብ የማይበቃው ዝርፊያ የማይሰለቸው ድርጅት፤ አሁንም በዚህ ሀውልት ስም ትርፍራፊ ለመልቀም ወደውጭ ማማተሩ አዲስ ነገር ሊሆን አይችል ይሆናል። ያው የተለመደውን ጎስቋላ ስደተኛ በማስፈራራት ይሁን በሌላ መልኩ ሊዘርፈው መዘጋጀቱ ግን መታወቅ አለበት። እናም እምቢኝ ለሀገሬ ማለት ባፍ ብቻ አይበቃም። የህዝብ መወገሪያ የሆነውን የኤኮኖሚ ምርኩዝ ላለማቀበል የወያኔን የኢኮኖሚ ምንጭ በሙሉ ለማድረቅ መዘጋጀት ያስፈልጋል። ከዚህ ሌላ ሁሉም ሊፈፅመው የሚችል በውጭ የሚደረግ ትግል አይኖርም።

እንዲህ አይነቱን ድርጊት ነው አንዳንድ የዋህ ሰዎች በመቻቻል እንለፈው በማለት ሊመክሩ የሚዳዳቸው። አጉል ምክር! አጉል ተቆርቋሪነት። ኢትዮጵያን የሚጎዳ ነገር ሲፈፀም ቆሞ የተመለከተ ሁሉ ተባብሮ እንዳጠፋት መቆጠሩን ግን አላጤኑትም። አቡነ ጴጥሮስ እንኳንስ ህዝቡ መሬቷ እንዳትገዛ ገዝቼአለሁ ያሉት ግፍና መከራ በበዛበት በፋሽስት ኢጣሊያ ዘመን ነበር። ወያኔ ለኢትዮጵያ አሳቢነቱ ከፋሽስቱ ኢጣልያ የተለየ ነው ብሎ ለማለት የሚደፍር ያለ አይመስለንም። ሁለቱም ከቀለማቸው በቀር አፍኖ ለመግዛት የሚያስችላቸው፤ መንገድ፤ ድልድይ፤ ግንብ ቤት በመስራት ይመሳሰላሉ። ህዝብን ጨፍጭፎ፤ እርስ በእርስ አጋጭቶ ለመግዛት በማሰብ ይመሳሰላሉ። ጣልያንም በባንዳ ወያኔም በሰላይ ካድሬ ስምሪት ይመሳሰላሉ። ኢጣልያ ግን ልግዛችሁ አለች እንጂ! ልሽጣችሁ ባለማለቷ ከወያኔ ትለያለች። በነዚህ ዘመናት ተባብሮ ያጨበጨበ፤ ጠላቱን ያደራጀ! ወገኑን የከዳ ልዩነት የለውም። ስለዚህም በውጭ ያለው ህብረተሰብ በመዋዛት የራሱን ወገን ማስገደያ ምሳር አቀባይ ከሆነ በፈቃደኝነት ወገኑን ለማስጨረስ ተዘጋጅቷል ማለት ነው። ፈቅዶ ማድረግና፤ ተታሎ ማድረግ፤ አንድ አይነት አይደሉም። ተታሎ የሚያደርግ ሰው እንደሰው የማሰብ ክብሩን ያስቀማ ነው። ፈቅዶ ያደረገ ግን

እንደመብት ሊቆጠርለት ቢችልም ምርጫው የተሳሳተ ነውና በጊዜው ማስተካከል የሚገባው ይሆናል።

ወያኔ ስርቆቱንም ማታለሉንም እያጠነከረው በመምጣቱ በቴሌፎን ካርድ ላይ ሳይቀር እየዘረፈ ይገኛል። ከካርዱ ሰሪዎችጋር በመስማማት በየጥሪው የተወሰነ ሳንቲም እየለቀመ መሆኑ ታውቋል። በተለይም <u>በቴሌ ኮም</u> ካርድ የሚጠቀሙ ሰዎች ሳያውቁት ለወያኔ ብዙ ሳንቲም እንደሚያስገቡ ተጋልጣል። ይህንን እያወቀ፣ እየሰማ፣ ከዚህ ዘረፋ ለኢትዮጵያ ህዝብ ይተርፈዋል ብሎ የሚያሰላ ኢትዮጵያዊ ካለ ዞር ብሎ ራሱን ይፈትሽ! እንጀራ ገዝቼ በመብላቴ የኢትዮጵያን ህዝብ አከብረዋለሁ ብሎ የሚያስብ ካለ ተጃጅሏል። በሁሉም መልክ ወያኔ እንጂ ህዝብ ሲያተርፍ አልታየምና!! ፕሮፌሰር አስራት በአንድ ወቅት እንዲህ ብለው ነበር “ ለወገን ውድቀትና መጠቃት ለሀገር መዋረድና መበታተን ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብት መታፈን መሳሪያ የሆኑ ሆዳም አማሮች ካሉ አጥብቀን እንመክራቸዋለን። በተለይም ወጣቱ የአባቶቹን ዓለማ ያለ ጥርጥር እንደሚያነሳ ሙሉ እምነት አለኝ” ነበር ያሉት። ሆኖም ባብዛኛው ወሬ ሲያራግብ የሚውለው፣ የትግል እንቅፋት እየሆነ ያለው ይኸው ሆዳሙ ክፍል ነው። አዋኸርዎች በሆዱ አሳበው ጥሪቱን ይዘርፉታል። በሀገር ፍቅር ስሜት ያነሆልሉታል። በወገን ፍቅር ሰበብ ያፎዙታል። ለዚህም ተግባር ልምድ ያላቸው አጭበርባሪዎችን አሰማርተውበታል። ስቀው የሚያሳስቁት፣ ተዋዝተው የሚያዋዙት፣ አልቅሰው የሚያባቡት፣ ወዳጅ መስለው የሚያሳስቱት፣ በባዶ ተጀንነው ተኮፍሰው ሰው የሚመስሉ፣ ሰው መሳይ ፍጡሮች ሁሉም አይነት ተመድቦለታል። ለማስገበር፣ ለማስጨብጨብ፣ በገዛ እጁ የመቃብር ጉድጓዱን እንዲቆፍር ለማስደረግ። ስለዚህም የተላከውን ሰው እንጂ የላከውን ባለመመልከት፣ ባለመጠርጠር፣ በርካታ ወገኖች የቅዠት እስር ቤት ውስጥ ይገኛሉ። ይህ ሊደበቅ አይችልም። ኢትዮጵያን እያስገደለ ወገኑን እያስጨፈጨፈ ያለው ሆዳም አማራው መሆኑ ሊደበቅ አይችልም።

የተከበራችሁ የአንዷት ኢትዮጵያ ልጆች!

ማንም ተቀየመ ማ! ይህንን መሳይ ትውልድ ገዳይ ድርጊት ሲፈፀም እያዩ ዝም ማለት በራሱ ወንጀል ነው። እነሱ ትውልድ ለመግደል ሲታገሉን እኛም ትውልድን ለማዳን መንቀሳቀስ ግዴታችን ነው። ኢትዮጵያን የሚጎዳ ነገር ሲደረግ ወገናችንን የሚያዋዛ ደባ ሲፈፀም፣ አድራጊው ያገር ልጅ ነው በሚል ሽፋን አድበን መመልከት አይገባም። “ለሌባ - ንሳው ጉድባ” ነው መባል የሚገባው። መጀመሪያ እራሱን ነፃ ያላወጣ ስለህዝብ መብት እታገላለሁ ቢል፣ ስለዲሞክራሲ፣ ስለፍትህ፣ ስለነፃነት አውቃለሁ ቢል ሀሰት ነው የሚሆነው። አስቀድሞ ስለሀገርም ሆነ ስለህዝብ ለማሰብ እራስን ከሌብነት ማፅዳት ያስፈልጋል። የህዝብ ገንዘብ እየዘረፉ፣ በህዝብ ጥቅም ላይ እየዶለቱ፣ ህዝብን በማጭበርበር በማያውቀው ድብቅ ሸር ውስጥ አስገብቶ በስሙ መነገድን ሳያቆሙ ወያኔን እቃወማለሁ ማለት ተራ ማጭበርበር ነው። የሀገር ተረካቢ ትውልድን የግል ሀብት ማካበቻ መሳሪያ ለማድረግ እየጣሩ ስለ ሀገር ማውራት አስቂኝ ነው የሚሆነው። በህዝብ ስም የሚገኘውን ገንዘብ እዚያው በዚያው እየተቀራመቱ፣ ስለወገን እናስባለን ብሎ ማለት ዘበት ነው የሚሆነው። ስለዚህም እንኳን ለአዲስ ዓመት አደረሳችሁ ሲባል! ይህ ሁሉ ርካሽ ጠባይ ያላቸው ግለሰቦች

ባዲስ ሁኔታ እራሳቸውን አስተካክለው እንዲገኙ ከመመኘት እንጂ! ሸርና ደባን ባዲስ መልክ ለማስፋፋት ያስችላቸው ለማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል።

ትግል ግልፅነትን ይጠይቃል። የኢትዮጵያን ህዝብ እንኳን አደረሰህ ማለት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ አለመሆኑ ቢታወቅም ስለመብቱ የሚታገሉለትን በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ እንኳን አደረሳችሁ ማለቱ ሀገራዊ ዘይቤ ነው። መጭው ዘመን የሀገራችን ህዝብ ከየድልደዩ ስር ወጥቶ፣ ማደሪያ ስፍራ አግኝቶ፣ ከበሽታ ከረሃብ ተላቆ፣ በባርነት የተሸጠው ከየሀገሩ ተሰባስቦ፣ በኢትዮጵያዊነቱ ተውቦና ተከብሮ። ያለፍርሃት በነፃነት በሀገሩ ጎዳና ሲንጎማለል የምናይበት ዘመን እንደሚሆን ጥርጥር የለውም!!! ዕድገቱ ሁሉ ከዚያ የሚመነጭ ነውና።

በኢትዮጵያ ላይ ያንዣበባት ደመና ይጠራል!
በህዝቡ ላይ የተጋረጠበት ጋሬጣ ይወገዳል!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

EthioLion.Com